የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
Ministry of Mines and Petroleum
Federal Democratic Republic Of Ethiopia

*የማዕድን ልማት ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሰረት*

# የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

ሐምሌ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ

## ማውጫ


የዘርፉ ርዕይ ............ iii

የዘርፉ ተልዕኮ ............ iii

የዘርፉ እሴቶች ............ iii

መግቢያ ............ 4

ክፍል አንድ ............ 6

1.2 የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም አጭር ግምገማ ............ 6

2.1. የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ............ 7

2.2. የ2014 በጀት ዓመት ዋና ዋና ፕሮግራሞች ግቦች እንዲሁም ታሳቢና............ 8

2.2.1. የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት ፕሮግራም ............ 8

2.2.2. የሥነ-ምድር መረጃን ለልማትና ኢንቨስትመንት የማመንጨት ፕሮግራም፣ ............ 9

2.2.3. የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የማጎልበት ፕሮግራም፣ ............ 11

2.2.4. የማዕድን እና ነዳጅ ምርት አቅርቦትና የአገር በቀል ኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም ግቦች ............ 122

2.2.5. የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትንና የአካባቢ ማህበረሰብን የማስተሳሰር ፕሮግራም፤ ............ 14

2.2.6 የ2014 በጀት ዓመት ዋና ዋና ፕሮግራሞች ግቦች እንዲሁም ታሳቢዎች ............ 8

የዘርፉ ዕቅድ አፈጻጸም ድጋፍ፤ ክትትልና ግምገማ አሠራሮች ............ 15

**የዘርፉ ርዕይ**

ኢትዮጵያ በ2022 ዘመናዊና ተወዳዳሪ የማዕድን ሀብት ተጠቃሚና የአፍሪካ ተምሳሌት፣

**የዘርፉ ተልዕኮ**

ግልጸኝነትን፣ ዘመናዊነትንና ተወዳዳሪነትን ያረጋገጠ የማዕድን ሀብት ልማት በማካሄድ ለአገራዊ ብልጽግና የካፒታል አቅም ማመንጨት ነው፡፡

**የዘርፉ እሴቶች**

ፍትሐዊነት

ግልጸኝነት

ተጠያቂነት

አሳታፊነት

ዓለም አቀፋዊነት

# መግቢያ

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት አስመዝግባለች። የኢኮኖሚ ዕድገቱን የሚያስቀጥል፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር መፍጠር እንዲሁም ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት ከ2012 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ወደ ስራ የገባ ሲሆን ባለፉት ሁለት ዓመታትም ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህም በመንግስት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በአንዳንድ መስኮች ብቻ የተመዘገበውን ዕድገት ወደ ሁሉን አቀፍ፣ የሰፊውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት የሚያጎለብት፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ አገራዊ የማይተካ ሚና እንደሚያሳድግ የተገኙት ውጤቶች አመላካቾች ናቸው፡፡

የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ቀዳሚ ትኩረት ከሰጣቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ አንዱ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመታት ዕውን ለምናደርገው አገራዊ ብልፅግና ከባድ ፈተና እንደሚሆን የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ለመፍታት የአንበሳውን ድርሻ የመውሰድ አቅም ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለሚሊዮኖች የስራ ዕድል መፍጠር የሚችል ሲሆን ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪና ሌሎች ዘርፎች የማዕድናት ግብአት ፍላጎትን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል ያልተነካ አገራዊ አቅም አለን፡፡

በማዕድን ዘርፉ ባለፉት በርካታ ዘመናት በርካታ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በውጭ ምንዛሪ ግኝትና ማዳን እንዲሁም ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ግብአት በማቅረብ ዘርፉ የጎላ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ሀገራችን ካላት ጂኦሎጂያዊና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና ረዥም ዘመናት ያስቆጠረች በመሆኗ ዓይነተ ብዙ የተፈጥሮ ሐብቶች መገኛ መሆኗን በአነስተኛ መጠንና የተካሄዱ ጥናቶችም አመላክተዋል፡፡

ከእነዚህ ማዕድናት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡- ወርቅ፣ ብር፣ ዚንክ፣ ፕላቲኒየም፣ ፖታሽ፣ ሰልፈር፣ ታንታለም፣ ብረት፣ መዳብ፣ ሊድ፣ ፎስፌት፣ የድንጋይ ከሰል፣ ኦይል ሼል፣ ዕብነበረድ፣ ግራናይት፣ የኖራ ድንጋይ፣ ባዛልት፣ ኳርትዝ፣ ካኦሊን፣ ፌልድስፓር፣ ዶሎማይት፣ ዳያቶማይት፣ ቤንቶናይት፣ ሶዳአሽ፣ ጅፕሰም፣ ጨው፣ ብሮሚን፣ ሲልካ ሳንድ፣ ክሮማይት፣ ሽክላ አፈር፣ ፑሚስ፣ የተፈጥሮ ጋዝ ይገኙበታል። ይሁን እንጅ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሟቸው ጥሬ ማዕድናት በሀገር ውስጥ የሚገኙ ቢሆንም የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ከውጭ ሀገር ይገባሉ። ይህም ሀገሪቱን ለአላስፈላጊ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ከመዳረጉም በላይ ልናገኝ የሚገባውን በርካታ ጥቅሞች አሳጥቶናል። በመሆኑም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ እነዚህና ሌሎች ማዕድናትን ተወዳዳሪ በሆኑ ዘዴዎች በጥልቀት በማጥናትና በስፋት ተመርተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ አገራዊ የብልፅግና ጉዟችንን ዕውን ማድረግ ይቻላል።

ይሁን እንጅ የማዕድናት ክምችት መኖርና በዕሴት ሳያበለፅጉ መጠቀም ብቻውን አገራዊ ዕድገትን የማያመጣ በመሆኑ የማዕድናት ዕሴት ማበልፀጊያ ተክኖሎጂዎችን በስፋት ማላመድ ያስፈልጋል፡፡ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴርም እነዚህን ዐቢይ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2014 በጀት ዓመት የዘርፉን አገራዊ ሚና የሚያጎለብቱ ግቦችን ወጥኖ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ2013 በጀት ዓመት አጠቃላይ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተሰጡ ግብረ-መልሶችን እንደ ግብዓት በመጠቀም ለታዩ ክፍተቶች አስፈላጊዉን የማስተካከያ ሥራዎች በማካተት የዘርፉን ርዕይ አንግቦ ተቋማዊ ተልዕኮ ለመፈፃም እንዲያስችል የቀጣይ አምስት አመታትን ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዘርፉ በአዲስ መልክ ተሻሽለዉ የተቃኙ ፕሮግራሞችን በ2014 በጀት ዓመት ለመተግበር በቂ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ፕሮግራሞች፡- የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት ፕሮግራም፣ የሥነ-ምድር መረጃ ለልማትና ለኢንቨስትመንት የማመንጨት ፕሮግራም፣ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንት የማስፋፋትና የማጎልበት ፕሮግራም፣ የማዕድንና ነዳጅ ምርት ማቅረብና የአገር በቀል ኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም እና የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትና የአካባቢ ማህበረሰብ ትስስር ፕሮግራም ናቸዉ፡፡ በተያዘዉ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች ከተጠናቀቀዉ የሁለተኛዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማስፈጸሚያ ፕሮግራሞች አንጻር ሲታዩ የፕሮግራሞች አሰያየም ብቻ ሳይሆን ዉጤት አመላካቾች (KPIs) ተገቢዉ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ በተለይም የፕሮግራሞች ዉጤት-ተኮር የሥራ አመራር ሥርዓት በመከተል ክትትልና ግምገማ የሚደረግ በመሆኑ ለአንድ ዉጤት አመልካች የሚያስፈልገዉ ግብዓትና አስፈጻሚ/ፈጻሚ አካላት በድርጊት መርሃ-ግብር የሚዘረዝሩ ሲሆን በዋናነት ሚኒስቴሩ፤ ተጠሪ ተቋማት፤ ክልሎች፤ ኩባንያዎች፤ ኢንተርፕራይዞችና አምራች ማህበራት ዋና ዋና ተዋናዮች ናቸዉ፡፡

# ክፍል አንድ

## የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም አጭር ግምገማ

በ2013 በጀት ዓመት ተቋማዊ የሪፎርም ስራዎቻችን የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የተሰጠውን ልዩ ተልዕኮ እንዲያሳካ ውጤታማ የሪፎርም ተግባራትን አከናውኗል፡፡ አላቂ የሆነውን የተፈጥሮ ሀብታችን ለዘላቂ የህዝባችን ጥቅምና የአገራችን ብልፅግና ጉዞ መሰረት እንዲሆን እንዲሁም ሃብቱን የማስተዳደርና የመምራት ተቋማዊ ብቃታችን ለማጎልበት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህ የሪፎርም ስራዎቻችን አንዱ ተቋሙ ለዓለማቀፍ ኩባንያዎች አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ግልጽ ቀልጣፋና ዘመናዊ ተቋም ለማድረግ እንዲሁም የሰራተኞችን የስራ ተነሳሽነትና በጋራ የመስራት ባህል ለማዳበር የቢሮ ዕድሳትና የምድረ ግቢ ማስዋብ ተግባራት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ተቋማዊ መረጃዎችና ሰነዶችን ዲጂታላይዝ የማድረግና ለአጠቃቀም ግልፅ፣ ምቹ፣ ቀላልና ተደራሽ እንዲሆኑ የማጠናቀቂያ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡

ከወጪ ንግድ ማዕድናት በአጠቃላይ ከ682 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከዘርፉ የተገኘ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ግብአት ምርቶችን በጥቂት አመታት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለመተካት የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያች ስራ ያቆሙ ኩባንያዎች ወደ ስራ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ለበርካታ ዓመታት በዘርፉ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው በርካታ ድጋፎች ቢደረግላቸውም በዉል ስምምነታችን መሰረት ወደ ስራ ያልገቡና ልዩ ልዩ ህጋዊ ግዴታቸውን ያልተወጡ የማዕድን ኢንቨስትመንት ፈቃዶችን አስፈላጊውን ሂደት በሟሟላት ውል የማቋረጥና ማስጠንቀቂያ የመስጠት ስራ ተከናውኗል፡፡ ውል የተቋረጠባቸው አካባቢዎች ለተሻለ የአገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች ኢንቨስትመንት እንዲውሉ መረጃዎችን በማደራጀት በተለያዩ ማዕድናት ላይ የፕሮሞሽን ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የዘርፉን የሰው ኃይል ብቁ፣ ተወዳዳሪና ሐብቱን በዕውቀት የሚመራ እንዲሆን ተቋማዊ አደረጃጀቱን በማስተካከል የመንግስትን ሐብት ከመቆጠብ ባሻገር ውጤታማ የሰው ሐይል ስምሪት ተፈጥሯል፡፡ ከዚህም ባሻገር ለ2014 በጀት ዓመት ውጤታማነት የሚያጎለብቱ የተለያዩ ማዕድን አለኝታ ፍለጋና ጥናትቶች ተከናውነዋል፡፡ ለዘመናት አገልግሎት ሳይሰጡ የተከማቹና የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጥረው የቆዩ ንብረቶችም የመንግስት አሰራር በጠበቀ መልኩ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ መደረጉ ትልቅ ስኬት ነው፡፡

በማዕድን ኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥና ውል አስተዳደር እንዲሁም ተዛማጅ ጉዳዮች ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ጥሩ ልምዶችን ካለፈው በጀት ዓመት የቀሰመ በመሆኑ በ2014 ዓ/ም የተሻለ አፈፃፀም እንደሚመዘገብ ይታመናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

የዘርፉ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በ5 ፕሮግራሞች የተዘጋጀ ሲሆን እንዚህም የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት፣ የስነ-ምድር መረጃን ለልማትና ለኢንቨስትመንት የማመንጨት፣ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የማጎልበት፣ የማዕድንና ነዳጅ ምርትን የማቅረብና የአገር-በቀል ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ እንዲሁም የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትንና የአካባቢ ማህበረሰብን የማስተሳሰር ፕሮግራሞች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ዕቅድ ሲሆን ለየፕሮግራሙ ስኬት አግባብነት ያላቸዉን ዉጤት አመላካች ተግባራትን (KPIs) እና ታሳቢ ጉዳዮችን አካቶ ቀርቧል፡፡

## 2.1. የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች

- ❖ የወጪ ንግድ ማዕድናትን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ
- ❖ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ማዕድናት በአገር ውስጥ ማድረግ
- ❖ ዘመናዊ የማዕድናት ግብይት ስርዓት መዘርጋት
- ❖ አገራዊ የማዕድን ሐብቶቻችን ላይ ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ዶክመንቶችን በማዘጋጀት ግዙፍ ኩባንያዎች በዘርፉ ማሰማራት
- ❖ የማዕድን ኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የኩባንያዎችን አቅምና ልምድ ያገናዘበ እንዲሆን
- ❖ ጠንካራ የፈቃድና የውል አስተዳደር ስርዓት መፍጠር
- ❖ በባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከክልሎች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል
- ❖ ከፍተኛ የማዕድናት ሐብት ባለባቸው አካባቢዎችና አገራዊ ፋይዳቸው በላቁ የማዕድን ኩባንያዎች አካባቢ የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮች እንዲቀረፉ በልዩ ትኩረት ይሰራል
- ❖ የዘርፉ የተማረ የሰዉ ኃይል ልማት በጥራትና ብዛት እንዲኖር ይሰራል
- ❖ ባህላዊ እና አነስተኛ የማዕድን አምራቾች ልዩ ትኩረት ይሰጣል
- ❖ አገራዊ የማዕድን አለኝታ መረጃን በዘመናዊ መልኩ ማደራጀት ተደራሽ ማድረግ
- ❖ የኢትዮጵያ ማዕድናት የብራንዲንግ ሥራ በማከናወን ዓለም አቀፍ እዉቅና እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤

## የ2014 በጀት ዓመት ዋና ዋና ፕሮግራሞች፣ ዉጤት አመልካች ተግባራት፣ ግቦችና ታሳቢዎች

### 2.2.1. የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት ፕሮግራም

የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማ የማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች ግልጸኝነት የሰፈነበት፤ ዘመናዊነትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለዉ እንዲሆን ተቋማዊ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም አድጎና በልጽጎ ለዘርፉ ዓበይት ተግባራት ዉጤታማነት የተሻሻለና ብቃቱ የተረጋገጠለት የመልካም አስተዳደር ችግሮች የቀነሱበት፤ ዘላቂነት ያለዉ ተቋም ማድረግ ነዉ፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ዉስጥ የሚተገበሩ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራት እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | የዉጤት አመልካች ተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ | 4ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የዘርፉን ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ አዋጆች፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ወደ ስራ ማስገባት | በቁጥር | -- | 31 | -- | 11 | 17 | 3 |
| 2. | በውጭና በአገር ውስጥ አጫጭር ስልጠናዎችን የትምህርት ዕድችን ለዘርፉ ባለሙያዎች ማመቻቸት | በቁጥር | 304 | 376 | 150 | 50 | 50 | 126 |
| 3. | በዘርፉ የሚገኙ ኢንቨስትመንትና ምርት ኢንዱስትሪዎችን እሴት ከሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር መፍጠር | በቁጥር | -- | 5 | -- | 2 | 3 | -- |
| 4. | ለዘርፉ ባለፈቃዶች የኢንቨስትመንት ችግሮቻቸዉን መፍታት | በቁጥር | 5 | 25 | 3 | 5 | 10 | 7 |
| 5. | የዘርፉን ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም በቢሮና በመስክ መከታተልና መገምገም | በቁጥር | 4 | 6 | 1 | 2 | 2 | 1 |

### 2.22 የሥነ-ምድር መረጃን ለልማትና ኢንቨስትመንት የማመንጨት ፕሮግራም፣

ይህ ፕሮግራም በዋናነት የሚተገበረዉ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሲሆን የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ መሠረታዊ የጂኦሳይንስ፣ የጂኦኬሚስትሪ፣ የጂኦፊዚክስ እና የሥነ-ምድር አደጋዎችን ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የልማት ሥነ-ምድር መረጃ ሽፋን፣ ጥራት እና ተደራሽነት በማሳደግ የግብርናን ምርት የሚያሳድጉ እና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚዉሉ ማዕድናት ፍለጋ ማካሄድ፣ ለመሠረተ ልማት የሚያገለግሉ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የዉጭ ምንዛሪ ለማፍራትና ለማዳን የሚያስችሉ

ማዕድናት ፍለጋ እና ጥናት ማካሄድ ነዉ። በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

| ተ.ቁ | የግብ አመላካች ተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የጂኦኬሚካል ሰርቬይ በ1፡1,000,000 መስፈርት ሽፋን | በመቶኛ | 70.26 | - | | | | |
| 2. | የአየር ወለድ ጂኦፊዚክስ ጥናት የፕሮጀክት ዶክመንት ዝግጅት ማከናወን | በመቶኛ | 0 | 100 | | | | 100 |
| 3. | የአፈር አሲዳማነት ለመከላከል የኢንዱስትሪ (ኖራድንጋይ) ማዕድን አለኝታ ፍለጋና ጥናት | በአለኝታ ቁጥር | 5 | 5 | | | | 5 |
| 4. | ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለውጪ ምንዛሪ ምንጭ የሚሆን የጌጣጌጥ (ጀምስቶን) ማዕድን አለኝታ ፍለጋና ጥናት በማከናወን ለተጠናበት ክልል መረጃውን ማስተላለፍ፣ | በአለኝታ ቁጥር | 4 | 5 | | | | 5 |
| 5. | ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለውጭ ምንዛሪ ምንጭ የሆኑ የደለል ወርቅ አለኝታ ቦታዎች በተለያዩ የአገሪቱ ክልል ፍለጋና ጥናት በማከናወን ለተጠናበት ክልል መረጃውን ማስተላለፍ፣ | በአለኝታ ቁጥር | 13 | 10 | | | | 10 |
| 6. | ከውጭ አገር የሚገባውን በመተካት ለአገር ውስጥ ጥቅም የሚውል የብረት አለኝታ ቦታዎች በተለያዩ የአገሪቱ ክልል የፍለጋና ጥናት በማከናወን ለተጠናበት ክልል መረጃውን ማስተላለፍ፣ | በአለኝታ ቁጥር | 4 | 4 | | | | 4 |
| 7. | ለማዳበሪያ፣ ለሲሚንቶ ማምረቻና ለኃይል ማመንጫ የሚያገለግል 1 የድንጋይ ከሰል አለኝታ ፍለጋና ጥናት በተለያዩ የአገሪቱ ክልል በማከናወን ለተጠናበት ክልል መረጃውን ማስተላለፍ፣ | በአለኝታ ቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 8. | በአገሪቱ የሬዲዮ አክቲቭ ሚኒራል (Uranium) ጥናትና ክምችት ግምት በየዓመቱ ማሳደግ | በአለኝታ ቁጥር | 3 | 4 | | | | 4 |
| 9. | የማዕድን አለኝታ ክምችት ቦታ ጥናቶች ብዛት | በቁጥር | 47 | 29 | | | | |
| 10. | የተደራጀ የማዕድናትን ክምችት ሃብት [መረጃ] | በመቶኛ | 10 | | | | | |
| 11. | በወርቅና ቤዝ ሜታል፣ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት፣ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ የግንባታ ማዕድናት ላይ ፈቃድ ከተሰጣቸው ኩባንያዎች ጋር በጋራ ማከናወን | በጥናት ቁጥር | 1 | -- | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12. | ለኢንተርፕራይዝ ልማትና መሰረተ ልማት ሥራዎች የሚውል የተጠኑ የሥነ-ምድር መረጃ በየዓመቱ በማሳደግ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ፤ | በቁጥር | 375 | 427 | | | | 427 |
| 13. | በማዕድናት አይነት ተለይቶ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የቀረበ የማዕድናት መረጃ | በቁጥር | 10 | 12 | | | 12 | |
| 14. | የመሬት መሰንጠቅ፣ የመሬት መንሸራተት፣ እና የጎርፍ አደጋ በኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች በማጥናት ካርታና ሪፖርቶች በየዓመቱ በማጥናት ለተጠቃሚ ዝግጁ ማድረግ፣ | በጥናት ሪፖርት ቁጥር | 5 | 8 | | | | 8 |
| 15. | በመሠረታዊ ጂኦሳይንስ (በ1፡50,000 በ1፡100,000 እና በ1፡1,000,000 መስፈርት) በየዓመቱ የሚጠኑ እና ለተጠቃሚ ዝግጁ የሚሆኑ ለማዕድን ፍለጋ፣ ለተለያዩ ጥናቶች መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች በየዓመቱ በማጥናት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ ማድረግ፤ | በጥናት ሪፖርት ቁጥር | 4 | 6 | | | | 6 |
| 16. | ከከርሰምድር ውሃ ሃብት ጥናት የተገኙ ለልማት ዝግጁ የሆኑ መረጃዎች በየዓመቱ (በ1፡50,000፣ በ1፡1,000,000 መስፈርት) በማጥናት ለዩኒቨርስቲዎች፣ ለክልል የግብርናና ውሃ ቢሮዎች የጥናት ሪፖርቱን ማቅረብ፤ | በጥናት ሪፖርት ቁጥር | 8 | 10 | | | | 10 |
| 17. | በክልል ዋና ዋና ከተሞችና በተለያዩ ዞኖች የተቆፈሩ የውሃ ጉዳጓዶች የውሃ ጥራትና ጥልቀት የክትትል ሥራ በበጋና ከክረምት በኋላ ማከናወን መረጃውንም ለአገር ውስጥ ጥቅም በየአመቱ በማሳደግ ለሚመለከተው መስጠት | በቁጥር | 0 | 2 | | | | 2 |
| 18. | ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ የተለያየ ሙቀት ያላቸውን የጂኦተርማል ኃይል እና ለቱሪዝም የሚሆን እሳተ ገሞራ አካባቢ ሃብቶችን ጥናት በቁጥር | በቁጥር | -- | 3 | | 3 | | |

## 2.2.2. የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የማጎልበት ፕሮግራም፣

የዚህ ፕሮግራም ዓላማ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት አቅም እና ልምድ ያላቸውን ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ በመሳብ የዘርፉ ልማት ለኢኮኖሚው አስተዋፀኦ እንዲያበረክት ማስቻል እና በዘርፉ ተሰማርተዉ የፕሮጀክት ሥራ እያካሄዱ ያሉ ባሀብቶችን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ልማትና ምርት ሥራዎች እንዲገቡ ማድረግ ነዉ፡፡

በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | የግብ አመላካች ተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በዘርፉን የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ዶክመንቶች ማዘጋጀትና ባለሃብቶች መሳብ | በሰነድ ቁጥር | 5 | 12 | 1 | 4 | 2 | 5 |
| 2. | ለዉጭ ባለሃብቶች አዲስ የሚሰጡ የማዕድን ምርመራና ምርት ፈቃዶች | በቁጥር | 12 | 20 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 3. | ለአገር ዉስጥ ባለሃብቶች አዲስ የሚሰጡ የማዕድን ምርምራና ምርት ፈቃዶች | በቁጥር | 11 | 66 | 10 | 18 | 25 | 13 |
| 4. | አዳዲስ የፔትሮሊየም ኢንቨስትመንት ስምምነቶች ማሳደግ፣ | በቁጥር | -- | 1 | -- | -- | 1 | -- |
| 5. | በነባር ማዕድን ኢንቨስትመንት የሚመዘገብ ካፒታል | በቢ.ሊየን ብር | 0.72 | 7.65 | 1.57 | 2.052 | 2.52 | 1.976 |
| 6. | አዲስ በሚሰጥ የፔትሮሊየም ፍለጋ/ልማትና ምርት የሚመዘገብ የኢንቨስትመንት ካፒታል | በሚሊዮን ዶላር | --- | 5 | | | 5 | |
| 7. | ለአዲስ የነዳጅና ነዳጅ ውጤቶች ማከፋፈያ ኩባንያዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት | በቁጥር | 301 | 256 | 49 | 68 | 70 | 69 |
| 8. | አዲስ ሥራ ላይ የሚውል የነዳጅ ተቋማትና ኩባንያዎች የኢንቨስትመንት ካፒታል | ሚሊዮን ብር | 937 | 4,928 | 939 | 1428 | 1322 | 1239 |
| 9. | በነባር የነዳጅ ተቋማት ላይ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች የምርት ጥራት ቁጥጥር ማድረግ | ቁጥር | 283 | 650 | 100 | 220 | 240 | 90 |
| 10. | የማዕድንና ነዳጅ ልማትና ኢንቨስትመንት ሥራዎችን የሚያግዙ በግሉ ዘርፍ የሚደራጁ የላቦራቶሪና የቁፋሮ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት መስጠት፣ | በቁጥር | 2 | 2 | -- | -- | 1 | 1 |
| 11. | በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት | በቁጥር | 11 | 16 | 3 | 4 | 5 | 3 |
| 12. | የግብይት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት | በቁጥር | 197 | 130 | 26 | 38 | 42 | 24 |
| 13. | በማዕድን ኩባንያዎች የሚፈጠር የስራ እድል | በቁጥር | 451 | 8626 | 1226 | 2800 | 2800 | 2000 |
| 14. | በፔትሮሊየም ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | በቁጥር | 1182 | 16500 | 4000 | 4000 | 4000 | 4500 |
| 15. | በሌሎች ዘርፎች የሚፈጠር የስራ እድል | በቁጥር | 529 | 500 | 100 | 150 | 150 | 100 |
| 16. | በክልሎች የሚሰጡ የባህላዊ/ ኢንተርፕራይዝ ፈቃዶች | በቁጥር | 5,560 | 6744 | 1686 | 1686 | 1686 | 1686 |
| 17. | በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚፈጠር የስራ ዕድል | በቁጥር | 108,333 | 255,299 | 63,824 | 63,825 | 63,826 | 63,824 |

## 2.2.3.የማዕድን እና ነዳጅ ምርት አቅርቦትና የአገር በቀል ኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም

የዚህ ፕሮግራም በዘርፉ በተሰማሩ ባለሀብቶችና በክልሎች በሚከናወኑ የማዕድናት፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ስራዎች ለገበያ እንዲቀርቡ ድጋፍ ለማድረግ በዚህም ሂደት የሚፈጠሩ ልዩ ልዩ የአገር ዉስጥ ገቢዎችን እና የወጪ ንግድ ማዕድናትን በመሸጥ የሚገኙ የዉጭ ምንዛሪ ገቢዎችን ለማሳደግ የተቀረጸ ፕሮግራም ነዉ፡፡

በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | የግብ አመላካች ተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በኩባንያዎች የሚመረት የወርቅ ምርት አቅርቦት መጠን | በኪ.ግ | 784.62 | 3991.031 | 997.76 | 739.625 | 739.625 | 739.625 |
| | በኩባንያ ለውጪ ገበያ በሚቀርብ የወርቅ ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 45.67 | 293.504 | 73.376 | 73.376 | 73.376 | 73.376 |
| 2. | በባህላዊ አምራች ማህበራት የሚቀርብ የወርቅ ምርት አቅርቦት መጠን | በኪ.ግ | 8467.35 | 10009 | 2502.25 | 2502.25 | 2502.25 | 2502.25 |
| | ለውጪ ገበያ ከሚቀርብ የወርቅ ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 572.4 | 736.071 | 184.02 | 184.02 | 184.02 | 184.02 |
| 3. | ለዉጭ ገበያ የሚቀርብ የታንታለም መጠን | በቶን | 56.6 | 100 | 24.99 | 24.99 | 24.99 | 24.99 |
| | በባህላዊ አምራቾች ተመርቶ ለውጪ ገበያ ከሚቀርብ የታንታለም ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 5.24 | 6.82 | 1.704 | 1.704 | 1.704 | 1.704 |
| 4. | በኩባንያዎች ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ዕብነ-በረድ መጠን | በሜ.ኩ | 3,178.84 | 5,000 | 900 | 1,384 | 1,454 | 1,226 |
| | ለውጪ ገበያ በሚቀርብ የዕብነ-በረድ ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 0.6 | 0.9626 | 0.17327 | 0.26645 | 0.27992 | 0.24296 |
| 5. | ሌሎችለዉጭ ገበያ የሚቀርቡ በከፊል የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት (ጥሬ እና እሴት የተጨመረበት ኦፓል) ምርት መጠን፣ | በኪ.ግ | 4,824.8 | 5500 | 1375 | 1375 | 1375 | 1375 |
| | ለዉጭ ገበያ ከቀረቡ ሌሎች በከፊል የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት (ጥሬ እና እሴት የተጨመረበት ኦፓል) ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 3.4159 | 7.083 | 1.7707 | 1.7707 | 1.7707 | 1.7707 |
| 6. | በባህላዊና ኢንተርፕራይዝ አምራቾች ለገበያ የሚቀርብ የጌጣጌጥ ማዕድናት መጠን፣ | በኪ.ግ | 25435.0981 | 123,895 | 30973.75 | 30973.75 | 30973.75 | 30973.75 |
| | በባህላዊ አምራቾች ተመርቶ ለውጪ ገበያ ከሚቀርብ የጌጣጌጥ ማዕድናት ምርት የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ | በሚ..ዶላር | 0.22851 | 1.09992 | 0.151725 | 0.151725 | 0.151725 | 0.151725 |
| 7. | ለዉጭ ገበያ የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ ማዕድናት መጠን፣ | በቶን | 3815.3 | 53095.55 | 13273.8875 | 13273.8875 | 13273.8875 | 13273.8875 |
| | ለዉጭ ገበያ ከሚቀርቡ የኢንዱስትሪ ማዕድናት የሚገኝ የዉጭ ምንዛሪ፣ | በሚ..ዶላር | 0.611 | 8.5036 | 2.1259 | 2.1259 | 2.1259 | 2.1259 |
| 8. | የውጪ ምንዛሪ ገቢ ጠቅላላ | በሚሊዮን ዶላር | 682.712 | 1054 | 263.5 | 263.5 | 263.5 | 263.5 |
| 9. | ለአገር ዉስጥ ገበያ በኩባንያ የሚቀርብ የጨው ምርት አቅርቦት፣ | በቶን | 25,000 | 250,000 | 62500 | 62500 | 62500 | 62500 |

| ተ.ቁ | የግብ አመላካች ተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10. | ለአገር ዉስጥ ገበያ በኩባንያ የሚቀርብ የባዛልት ምርት፣ | በቶን | 11.988 | 416,250 | 104,063 | 104,063 | 104,063 | 104,063 |
| 11. | ለአገር ዉስጥ ገበያ በኩባንያ የሚቀርብ የሸክላ አፈር ምርት፣ | በቶን | -- | 44,925.6 | 11,231.4 | 11,231.4 | 11,231.4 | 11,231.4 |
| 12. | በኩባንያ ለአገር ዉስጥ ገበያ የጂፕሰም ምርት አቀርቦት፣ | በቶን | -- | 173,972 | 43,493 | 43,493 | 43,493 | 43,493 |
| 13. | ለአገር ዉስጥ ገበያ በኩባንያ የሚቀርብ የላይምስቶን ምርት፣ | በቶን | -- | 3,823,194.96 | 955,798.7 | 955,798.7 | 955,798.7 | 955,798.7 |
| 14. | ለሀገር ውስጥ ገበያ በኩባንያ የሚቀርብ የዕብነበረድ ምርት፣ | በሜ.ኩ | 15,090.24 | 83,250 | 20,812.5 | 20,812.5 | 20,812.5 | 20,812.5 |
| 15. | ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የቀረበ የማዕድናት ግብዓት ምርት ሽያጭ | በሚ.ብር | -- | 1012.7 | 253.17 | 253.17 | 253.17 | 253.17 |
| 16. | በክልሎች የሚቀርብ የግንባታ ማዕድናት ምርት መጠን | በሚ. ሜ.ኩብ | 28.1 | 46.02 | 11.505 | 11.505 | 11.505 | 11.505 |
| 17. | በክልሎች የሚቀርብ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት መጠን | በሚ. ቶን | 4.9 | 6.4 | 1.6 | 1.6 | 1.6 | 1.6 |
| 18. | ከማዕድን የሚገኝ የሮያሊቲ ገቢ | በሚ.ብር | 36.5 | 505.32 | 126.33 | 126.33 | 126.33 | 126.33 |
| 19. | ከማዕድን ስራዎች የሚሰበሰብ ልዩ ልዩ ገቢ (ከሮያሊቲ ዉጭ) | በሚ.ብር | 0.6748 | 1.755 | 0.412 | 0.472 | 0.472 | 0.412 |
| 20. | በክልሎች ከማዕድን ሥራዎች የሚሰበሰብ ልዩ ልዩ ገቢ | በሚ.ብር | 306.23 | 568.03 | 142 | 142 | 142.1 | 142 |
| 21. | የማዕድን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ዕድገት | በመቶኛ | -- | 3 | | | | |
| 22. | የማዕድን ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ምርት ድርሻ | በመቶኛ | -- | 0.2 | | | | |
| 23. | ከማዕድን ዘርፍ የወጪ ንግድ የሚገኝ ገቢ ጠቅላላ የሸቀጦች ወጪንግድ ገቢ ያለው ድርሻ | በመቶኛ | 17 | 25.3 | | | | |
| 24. | የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ዕሴት የሚጨምሩ ኢንዲስትሪዎችን ቁጥር ማሳደግ | በቁጥር | -- | 5 | | | | |
| 25. | የኮንስትራክሽን ግብአት አምራች ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር ማሳደግ | በቁጥር | --- | 248 | | | | |
| 26. | ለኬሚካል፣ፔትሮኬሚካል ምርት የሚረዱ ማዕድናትን በማምረት ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር ማሳደግ | በቁጥር | -- | 58 | | | | |
| 27. | የሃይል አምራች ኢንደስትሪዎች እንድስፋፉ ማድረግ | በቁጥር | 1 | 1 | | | | |
| 28. | ከማዕድን፣ ከነዳጅ እና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎቶች የዋለው ድርሻ | በመቶኛ | -- | | | | | |

## 2.2.4. የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትንና የአካባቢ ማህበረሰብን የማስተሳሰር ፕሮግራም፤

የዚህ ፕሮግራም ዓላማ የባለፍቃዶችን የሙያ ጤንነትና ደህንነት አፈጻጸም በመከታተል በማዕድን ልማት አካባቢና በማህበረሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዳይኖሩ/እንዲቀንሱ እንዲሁም በልማቱ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ልማቱን ከአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ፍላጎት ጋር የተጣጣመና ዘለቄታዊ ማድረግ ነው። በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

| ተ.ቁ | የግብ አመላካችተግባራት | መለኪያ | መነሻ አመት የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም | የ2014 በጀት አመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የማዕድንና ፔትሮሊየም ኢንቨስትመንት ሥራ አካባቢ ከብክለት የፀዳ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በፈቃድ ቁጥር | 43 | 154 | 20 | 30 | 52 | 52 |
| 2. | በማዕድን እና ነዳጅ ኢንቨስትመንት አካባቢዎች የአረንጓዴ ሽፋንን ማሳደግ | በሄክታር | 44 | 50 | 12 | 13 | 12 | 13 |
| 3. | ከማዕድንና ነዳጅ በውል ስምምነት መሰረት የሚሰበሰብ የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ፈንድ | በሚሊየን ብር | 89.5 | 64 | 16 | 16 | 16 | 16 |
| 4. | ከማዕድንና ነዳጅ ባለፈቃዶች በውል ስምምነት መሠረት የተሰበሰበውን የማህበረሰብ ልማት ፈንድ ወደ ተግባር ማስገባት | በሚሊየን ብር | 47.74 | 40 | -- | 10 | 10 | 20 |

# ለዕቅዱ ተፈፃሚነት ታሳቢ የተደረጉ ሁኔታዎች

በአምስቱም ፕሮግራሞች የተወጠኑ ግቦች በማሳካት የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ከማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ የሚጠብቃቸውን ውጤቶች ዕውን በማድረግ አገራዊ የብልፅግና ጉዞ ለማረጋጥ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት ባሻገር ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት የማይተካ ሚና ይጠበቃል። በመሆኑም

- መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል፣
- የማዕድናት ሐብት በስፋት የሚገኝባቸው አካባቢዎችና አገራዊ ፋይዳቸው ላቅ ያለ በሆነ የማዕድን ኩባንያዎች አካባቢ የሚስተዋለው የፀጥታ ችግር እንደሚቀረፍ፣
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያደረገዉ የወርቅ ቅበላ ዋጋ ማሻሻያ አቅራቢዎችንና አምራቾችን እንዲበረታቱ በማድረግ የተሻለ የወርቅ ምርት ለባንክ እንዲቀርብ በማድረጉ ማበረታቻዉ እንደሚቀጥል፤
- የዘርፉን አሰራር ተወዳዳሪ ለማድረግ የተዘጋጁ የህግ ማዕቀፎች በወቅቱ እንደሚፀድቁ ታሳቢ ተደርጓል።

# ክፍል ሦስት
# የዘርፉ ዕቅድ አፈጻጸም ድጋፍ፤ ክትትልና ግምገማ አሠራሮች

የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ዉጤታማ ለማድረግ ለእያንዳንዱ ፕሮግራም አፈፃፀም የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥራ በማከናወን ግብረ-መልስ የመስጠትና ክፍተቶችን የማስተካከል ስራዎች ይሠራሉ፡፡ በዚህም፡-

- የዘርፉን ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስራዎች በየሩብ ዓመቱ በማከናወንና ግብረ-መልስ በመስጠት በሚታዩ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡
- የማዕድን ምርትና ግብይት ስራዎች ውጤታማነትን ለማጎልበት የሚረዱ ዘመናዊ አሰራሮች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል
- በዘርፉ የታቀዱ ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ በመንግስት የተመደበ የመደበኛና ካፒታል በጀት እንዲሁም ከአጋር አካላት በድጋፍ የተገኘ በጀት ለታለመለት አላማ ስለመዋሉ በየሩብ አመቱ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በክትትልና ግምገማዉ የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል የበጀት ማስተካከያ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ ክፍለ-ኢኮኖሚ ለአገራዊ ዕድገትና ብልጽግና ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በበጀት ዓመቱ በተከናወኑ የሪፎርምና መደበኛ ስራዎች አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በአፈፃፀም ሂደት የነበሩ ክንዋኔዎችን በጥንካሬና በድክመት እንዲሁም በቀጣይ ትኩረት በሚሰጣቸው የዘርፉ ዐቢይ ትልሞች ላይ ሰራተኞችን፣ የሕዝብ እንደራሴዎችን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማወያየት ለ2014 በጀት አመት ዕቅድ ግብዓት የሆኑ ሐሳቦችና አሰራሮች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በቀጣይ 2014 በጀት አመት በዘርፉ ፕሮግራሞች፣ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራና ግቦች እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶችን የበለጠ እንዲጎለብቱ ከተጠሪ ተቋማት፣ ከክልሎችና ከከተማ መስተዳደር የዘርፉ የመንግስት መ/ቤቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የማዕድንና ነዳጅ ክፍለ-ኢኮኖሚዉ በአገራዊ ጥቅል ምርት ላይ ያለዉን ፋይዳ ለማሳደግ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡